# «ተቃዋሚዎች መጠንከር፣ መተባበርና ኃይል መሆን መቻል አለባቸው»

አቶ ስዩ አብርሃ

አቶ ስዬ አብርሃ ከእስር ቤት ከወጡ በኋላ መድረክ በተባለው የፓርቲዎችና የታዋቂ ግለሰቦች ስብስብ ውስጥ መሳተፍ ጀምረዋል፡፡ በስብስቡ መሳተፍ ከጀመሩም በኋላ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች አቅርበዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ እሳቸው «አማካይ ስፍራ» በሚሉት የፖለቲካ አቋም በብሔር የተደራጁና በሕብረ ብሔር የተደራጁ ፓርቲዎች በሚያግባባቸው የጋራ አቋሞች ዙሪያ እንዲሰባሰቡ ግፊት በማድረግ ሳይ ናቸው፡፡

እኛም እሳቸው እያራመዱት ስላለው የፖለቲካ አቋም፤ ኢትዮጵያ ከጐረቤት አገሮች ጋር ስላላት ግንኙነት፣ ኢትዮጵያ ተፋሰሶቿን በአግባቡ ለመጠቀም ምን ማድረግ እንዳለባትና በመጪው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ ስለሚጠበቀው ምርጫ ዙሪያ አነጋግረናቸዋል፡፡

**<u>ሰንደቅ</u>፡-** በቅርቡ የሱዳኑ ፕሬዝዳንት በግብፅ፣ በኤርትራ ሰሞኑን ደግሞ በኢትዮጵያ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በዚህ ረገድ ሱዳን ከኤርትራም ሆነ ከኢትዮጵያ ጋር ያላት የጉርብትና ወዳጅነት ምን ያህል ዘላቂና የተረጋጋ ነው ይላሉ?

**<u>አቶ ስዩ አብርሃ</u>፡-** *የሱዳንና የኢትዮጵያ ግንኙነት የሁለት አገሮች ግንኙነት ነው፡፡ አፄ ኃይለስላሴ እያሉ፣ ደርግም እያለ ኢሕአዴግም እያለ የማይቀየሩ እውነታዎች አሉ፡፡ ሱዳን ጐረቤት ሀገር ናት፡፡ በሁለታችን መካከል ትልቅና ሰፊ ድንበር አለ፡፡ ሱዳን የአባይ ወንዝ ተጠቃሚ ሀገር ናት፡፡ ግብፅም እንዲሁ የአባይ ውሃ ተጠቃሚ ሀገር ናት፡፡ እና ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት እንዳላት ሁሉ፤ ከግብፅም ጋር ግንኙነት እንዳላት መገንዘብ ይኖርብናል፡፡*

*በውሃ ጉዳይ ሦስታችንንም የሚያያይዙን ጉዳዮች እንዳሉ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ስለሆነም የሱዳንና የኢትዮጵያ ግንኙነት ከውሃም ጋር ይያያዛል፡፡ እናም አንዳንድ ጊዜ ሞቅ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በረድ ይላል፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜ ከመሰረቱ ያለው ውሃ ነው፡፡ ውሃው ደግሞ ሦስቱንም አገሮች የሚያነካካ መሆኑ፤ አብዛኛው ውሃ ከኢትዮጵያ የሚፈስ መሆኑ፤ ኢትዮጵያ ውሃውን ለመጠቀም መብትም ጥያቄም ያላት ሀገር መሆኗ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘም ሱዳንና ግብፅ በዚህ የኢትዮጵያ ፍላጐትና ጥቅም ላይ ይቀነስብናል የሚል ስጋት ያለ በመሆኑ ጥንቃቄ የበዛበት ግንኙነት እንዳላቸው ለመረዳት አያስቸግርም፡፡*

*ስለዚህ የፍቅርና የወዳጅነት የሚባለው ነገር ሳይሆን የራስን ጥቅም አስከብሮ በመሀሉ ደግሞ የጋራ ጥቅም የመገንባት ጉዳይ እንጂ፤ ዘለቄታ ብሎ ነገር እንዲሁ ዝም ብሎ የሚመጣ*

ነገር አይደለም። ሁለቱ መሪዎች ስለተዋደዱ ወይም ስለተሳሳሙ ብቻ ግንኙነቱ በጠንካራ መሠረት ላይ ቆሟል ማለት አይደለም።

በሌላ በኩል የሱዳን መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት እንዳለው ሁሉ ከኤርትራም ጋር ግንኙነት ቢኖረው አይገርምም። አንደኛ የሚጋሩት ነገር አላቸው። ሁለተኛ ኤርትራና ኢትዮጵያ ተጣላንም አልተጣላንም ሱዳኖች ከኤርትራ ጋር መደበኛ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማድረጋቸው አግባብ ነው። ስለዚህ ከአባይ ጋር ያለው ስጋት ሱዳንና ኤርትራን ቢያቀራርባቸው አይገርምም። ሻአቢያ ደግሞ ሽር ይፈልጋል። ኢትዮጵያ እንድትዳከም ይፈልጋል። ኢትዮጵያ እንድትለማ አይፈልግም። መልማት ማለት ደግሞ ውሃ መገደብና መስኖ መስራት ማለት ነው። ስለዚህ ሻአቢያ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውሃ ገድባ እንዳትጠቀም የሚፈልጉ ሌሎች አገሮች አሉ። ስለሆነም ይሄንን ሁኔታ ከማሳካት አንፃር ሱዳኖች ኤርትራን ሊፈልጓት ይችላሉ። በመሆኑም እያንዳንዱ ሀገር የየራሱን ጥቅም እያሰላ ነው ግንኙነቱ የቀጠለው።

**<u>ሰንደቅ</u>፦ በአገሮቹ መካከል በተለይም በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ ህዝብ ለህዝብ ደረጃ አውርዶ በጋራ ጥቅም ላይ ለመመስረት ምን ያህል ርቀት ተሄዷል ብለው ያምናሉ?**

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>፦** እውነት ለመናገር ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር ጠንካራ ወዳጅነት በመመስረት ከራሷ ብሔራዊ ጥቅም አኳያ የበለጠ ትጠቀማለች። ኢትዮጵያ ወንዞቿን ብትገድብ ሱዳን ትጠቀማለች እንጂ አትጐዳም። የተቀነሰ ቢቀነስም ሱዳን በፍፁም የውሃ እጥረት አይገጥማትም። ይልቁንም የጋራ ድንበር ስላለን አንድ ቦታ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰራው ግድብ ከዛ የሚገኘው የመስኖ ትሩፋት ድንበር ተሻግሮም ሊሄድ ይችላል። መስኖዎቹም ድንበር ተሻጋሪ ሊሆኑም ይችላሉ። ወንዞቹ ድንበር ተሻጋሪ እንደሆኑ ሁሉ ኩታ ገጠም ድንበር ያለን በመሆኑ መስኖዎች ድንበር ተሻጋሪ ማድረግ ይቻላል። በኤሌክትሪክ በኩል ከመጣንም ሱዳን የበለጠ ተጠቃሚ ትሆናለች። ስለሆነም በአባይ አጠቃቀም ዙሪያ ከግብፅ ጋር የሚጋሩት ስሜትና ስጋት ቢኖርም የኢትዮጵያ ወንዞች በጥቅም ላይ ቢውሉ ሱዳን የበለጠ ትጠቀማለች እንጂ አትጐዳም። ይሄም ሆኖ ለብዙ አመታት የቆዩ ፍርሃቶችና ስጋቶች በአንድ ጊዜ አይቀረፉም። በንግግርም፣ በቃልም፣ በፊርማም አይቀረፉም።

ነገር ግን ከላይ በጠቀስኳቸው እሴቶች ዙሪያ ድልድይ መፍጠር ያስፈልጋል። ግድቦች ተሰርተው ኤሌክትሪክ ሲያገኙ፣ ግድቦች ተሰርተው ድንበር ላይ ያለው የሱዳን መሬት ሲለማ፣ መንገዶች ሲከፈቱ፣ ከኢትዮጵያም ሆነ ከሱዳን የሚዋሰኑ ሰፋፊ ለም መሬቶች በመስኖ ሲለሙና ሲሰለጥኑ በአዋሳኝ አካባቢ ያለው ሰፊና ለም መሬት ለምቶ ብዙ ሰው ለመኖሪያነት ሲመርጠውና ሲሰለጥን የግድ የህዝብ ለህዝብ መተሳሰሩ የጠነክራል።

በአሁኑ ወቅት ያለው ግንኙነት ከጐንደር ገዳሪፍ ብቻ ነው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚስተዋለው። በመሀል ላይ ያለው ግንኙነት ግን ደካማ ነው። ያም ሆኖ ሱዳኖች ኢትዮጵያ ውሃውን ለማልማት የምታደርገውን ጥረት በሙሉ ድጋፍ እንጀራችን፣ ጥቅማችን ከኢትዮጵያ

ነው ብለው፤ እንዲያስቡ ለማድረግ ቀላል አይደለም:: ለብዙ ጊዜ የቆየውን አስተሳሰብ በአንድ ጊዜ መሻር አይቻልም::

**<u>ሰንደቅ</u>:-** በአሁኑ ወቅት ደቡብ ሱዳንን ራሱን ችሎ እንደ ሀገር ለመመስረት አንዳንድ ምልክቶች እየታዩ ነው:: ምልክቶቹ ነፍስ ዘርተው ደቡብ ሱዳን እንደ ሀገር ብትመሰረት በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ ያለ ይመስሎዎታል?

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>:-** የደቡብ ሱዳን እንደ ሀገር መመስረት የሚወሰነው በደቡብም በሰሜኑም የሱዳን ህዝብ ውሳኔ ነው:: ደቡብ ሱዳን ተለይቶ የራሱን መንግሥት ያቋቁማል ወይ አንድ ነገር ነው:: እኛ የምንፈልገው ግን ሠላም ነው:: ሱዳን አንድም ሆነ ሁለት እኛ ሠላም ነው የምንፈልገው:: ነገር ግን ደቡብም ተለይቶ ሠላም ይኖራል ወይ? የሚለው ዋና ጉዳይ ነው:: እኛ ሠላም እስካገኘን ድረስ የቀረው የደቡብ ሱዳን የራሱን መንግሥት የማቋቋም ጉዳይ የራሳቸው የሱዳኖች ውስጣዊ ጉዳይ ስለሆነ ውሳኔአቸውን እናከብራለን:: እና በእኛ ላይ ምን ያህል ጫና ያሳድራል ብሎ አሁን ላይ ሆኖ ለመገመት ይቸግራል:: ደቡብ ሱዳኖች እንለይ ቢሉ ምን ያህል አስተማማኝ ሠላም ይኖራል? ብሎ ለመጠየቅ ያስችላል:: አካባቢው በውሃ ጠቀሜታ ላይ ከፍተኛ ስጋት ባለበት ሁኔታ ሌላ ሀገር ሲጨምር ሠላም ይወርዳል ወይ? ብሎ ማሰብም ይጠይቃል:: ያም ሆኖ ለእኛ ለኢትዮጵያን ሱዳኖች ሁለትም ሆኑ አንድ ሠላማዊ ጉርብትና እንዲኖር ነው የምንፈልገው::

**<u>ሰንደቅ</u>:-** ወደ ሶማሊያ ልውሰድዎና ሰሞኑን አስመራ ለሁለት አመት የቆየት ሼህ ዳሂር አዌይስ ወደ ሶማሊያ ተመልሰዋል:: የዳሂር አዌይስን ወደ ሶማሊያ መመለስ የተገነዘቡ ወገኖች ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ላይ ስጋት የሚፈጥሩ ኃይሎች ተመልሰው እንዳያንሰራሩ ስጋት እንዳለ ይገልፃሉ፣ ሁኔታውም «ታጥቦ ጭቃ» ይሆናል ብለው የሚሰጉ ሰዎች ስላሉ በዚህ ረገድ የእርስዎ አስተያየት ምንድነው?

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>:-** በቅድሚያ የታጠበስ ጭቃ ነበር ወይ? የሚለው መታየት አለበት:: ታጥቦ የተጠረገ ጭቃ ነበር ወይ? ታጥቦ የተጠረገ ጭቃ ካለ ጭቃው እንዳይመለስብኝ ብለህ ልትሰጋ ትችላለህ:: ነገር ግን ጭቃ ነበር ወይ? ከዚህ በፊትም እንደተናገርኩት አሁን የሶማሊያ ፕሬዝዳንት ሆነው ያሉት ሰውዬ የእኛ ሠራዊት ሞቃዲሾ ከመግባቱ በፊት ከአዌይስ ጋር ነበሩ:: አዌይስ ከመመለሳቸውም በፊት የእኛ መከላከያ ሠራዊት ሳይገባ በፊት የነበረው ሁኔታ ነው አሁን የተፈጠረው:: አዌይስ ወደ ሞቃዲሾ ስለተመለሱ የሚለወጥ ነገር አለ ብዬ ለመገመት እቸገራለሁ::

ዋናው ነገር ሸህ ሸሪፍ እና አዌይስ ለኢትዮጵያ ስጋት ይሆናሉ ወይ? ከተባለ አይሆኑም ነው መልሱ:: ድሮም ቢሆን በሶማሊያ በኩል ኢትዮጵያ የሚመጣበት ስጋት እንዳለ ይታወቃል:: ይሄ ደግሞ የቆየ ስጋት ነው:: ሲያድባሬ እያሉና ከዚም በፊት በሶማሊያ በኩል በኢትዮጵያ ላይ የማነጣጠር ሁኔታ አለ:: አቅም ያገኙ ጊዜ ሲያድባሬ ኢትዮጵያን የወረሩበት ሁኔታ አለ:: አቅም ያጡ ጊዜ ኢትዮጵያን ለመጉዳት ማለማቸው አይቀርም:: አልመዋል ብለን መድፍና ታንክ ይዘን መግባት ይኖርብናል ወይ? ነው ጥያቄው:: መጠበቅ መከላከል ተገቢ ቢሆንም ደረጃ፣ መልክ እና

ቅጥ አለው:: ያም ሆኖ አሁን ሠራዊታችንም ወደ ድንበሩ ተመልሷል:: አዋይስም ተመልሶ ወደ ሶማሊያ ገብቷል:: ስለዚህ የራሳችንን ድንበር አጥብቆ መጠበቅ ስጋት ይጨምራል፣ ይቀንሳል እያሉ በትናንሽ ነገሮች ከመሯሯጥ ድንበራችንን መጠበቁ የተሻለ ይሆናል::

**ሰንደቅ**:- በኢትዮጵያ መንግሥት አገላለፅ፤ «ፀረ ሠላም ኃይሎች ... ተላላኪዎች» የሚባሉ ኦነግና ኦብነግን የመሰሉ ድርጅቶችም የሶማሊያን አለመረጋጋት እንደ ከለላ በመጠቀም ከኤርትራ መንግሥት ጋር በጋራ በመሆን ኢትዮጵያን ያተራምሳሉ የሚል ስጋት ይነሳልና ይሄንንስ ስጋት እርስዎ እንዴት ይረዱታል?

**አቶ ስዬ አብርሃ**:- ይሄኛውን ስጋት የሀገር ውስጥ ፖለቲካን በማስተካከል የሚፈታ ስጋት ነው:: ድንበር ጠብቆ የሚቀር ስጋት ቢኖርም፤ የሀገር ውስጥ የፖለቲካ ስጋት ግን ድንበር በመጠበቅ አይፈታም:: የሀገር ውስጥ የፖለቲካ ስጋት ሊፈታ የሚችለው በውይይት፣ በመግባባት መንፈስ በድርድርና በሠላማዊ መንገድ ነው የሚፈታው::

**ሰንደቅ**:- የኤርትራ መንግሥት የጅቡቲን መሬት «በሕገ-ወጥ» መንገድ መቆጣጠሩን የተባበሩት መንግሥታት አረጋግጧል:: የኤርትራ መንግሥት በጅቡቲ ላይ የወሰደው እርምጃ የጅቡቲን ወደብ ሙሉ በሙሉ እየተጠቀመች ባለችው ኢትዮጵያ ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ እስከምን ደረጃ ሊዘልቅ ይችላል?

**አቶ ስዬ አብርሃ**:- ሻአቢያ አቅም ይኖረዋል ወይ? የሚለው በቅድሚያ ሊታይ ይገባዋል:: ሻአቢያ አቅም እስካለው ድረስ አይመለስም:: በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን ማወኩ አይቀርም:: ነገር ግን የማወክ ችሎታው ምን ያህል ነው? ዋናው ነገር የማወክ ችሎታ የለውም::

ያም ሆኖ በጅቡቲ ድንበር ላይ የሚነሳ ውዝግብ ሁከትና አለመረጋጋት ብዙ ቀንድ ያለው ጥያቄ ይመስለኛል:: በእርግጥ የኤርትራ መንግሥት አቅሙን ለጅቡቲ ለማሳየት አስቦ ይሆናል:: ነገር ግን ሻአቢያ ምንም ኃይል የለውም:: ትንሽም ኃይል ካለው ጠመንጃ ነው:: ስለዚህ የዲፕሎማሲውን ጨዋታ ሁልጊዜ ጠመንጃ በማሳየት ነው መጫወት የሚፈልገው:: ሱዳንም ለማስፈራራት ተቃዋሚዎችን አስታጥቆ ይለቅባቸዋል:: ወደ ኢትዮጵያንም ተቃዋሚ የሚባሉ ፈጥሮ የመላክ ስትራቴጂ አለው:: በጅቡቲ ደግሞ በራሱ «አሳይሻለሁ» ብሎ ገብቶበታል:: ስለሆነም የመጫወቻ ካርዱ ጠመንጃ ነው:: እና ጅቡቲም ላይ ጦር ያዘመተው መጫወት የፈለገው የዲፕሎማሲ ጨዋታ በመኖሩ ይሆናል::

በእርግጥ ያ አካባቢ በጣም የተወሳሰበ ቦታ ነው:: ቦታው በጣም ጠባብ ስለሆነ ትላልቅ መርከቦችን ሊያሳልፍ የሚችለው የውሃ መንገድ ጠባብ ነው:: እና የጅቡቲን መሬት በዛ በኩል ይዞ የተቀመጠው ተኩስ ከሚደርስበት ቦታ ለመቀመጥ አስቦ ይሆናል:: በዚህ ረገድ በአካባቢው የኢራን መግባትን አስመልክቶም የሚወራ ወሬ አለ:: ኢራኖች አሰብን ሲይዙ በጅቡቲ በኩል የኤርትራን ዘብ ማስቀመጥ ፍላጐት ሊኖር ይችላል:: ስለዚህ በኢትዮጵያ፣ በጅቡቲና በመተላለፊያው መስመር ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ በዚህ መልኩ ሊታይ ይችላል::

**<u>ሰንደቅ</u>፡-** ኢትዮጵያ ተፋሰሶቿን በአግባቡ በመጠቀም፤ ከድህነት እንድትወጣ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጥረቶች ሲጀመሩ አንዳንድ እንቅፋቶች ሲያጋጥሙ ይታያል፡፡ እንደ ምሳሌ ግልገል ጊቤ 3ን ማንሳት ይቻላል፡፡ እና መቼ ነው ሀገሪቱ ተፋሰሶቿን በአግባቡ ተጠቅማ ከድህነት የምንወጣው?

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>፡-** ኢትዮጵያ ተፋሰሶቿን ካለተጠቀመች በኢትዮጵያ ረሀብ አይጠፋም፡፡ ዝናብ መጣ ቀረ እየተባለ ይሄን ያህል ማዳበሪያ ታደለ እየተባለ በዜና እየተነገረ ድህነት አይጠፋም፡፡ የድህነት ማጥፋት ዜና ሊሆን የሚገባው ኢትዮጵያ በየአመቱ ይሄን ያክል ሺህ ሔክታር በመስኖ አለማች ሲባል ነው፡፡ ዜናም ብቻ ሳይሆን እንደዚህ አይነት ግብ መጣል ያስፈልጋል፡፡ በየአመቱ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሔክታር በመስኖ እናለማለን ብሎ ይሄው አንድ መቶ ሺህ አልምተናል፡፡ እንደገና በቀጣዩ አመት ደግሞ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ አሳድገናል፣ በሚቀጥለውም በዚህን ያህል ፐርሰንት አድጓል ሲባል እራሱ እድገቱ የማይቀለበስ ይሆናል፡፡ ረሃብ አይደለም የኢኮኖሚ እድገቱ የማይቀለበስ ይሆናል፡፡ ነዳጅ ጨመረ ... የሐዋላ ገንዘብ አነሰ ... የውጪ እርዳታ ተቀነሰ ... ወዘተ እየተባለ የማይቀለበስ በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ የልማት እድገት ይሆናል፡፡

መስኖ ሲባል ውሃ ማቆር አይደለም፡፡ ላስቲክ አንጥፎ ጉድጓድ ቆፍሮ ውሃ ማቆር፣ ከዛ ይሄን ያህል ጉድጓድ ተቆፈረ አይደለም የልማት ዜና፡፡ ተፋሰሶቻችንን መገደብ ነው መፍትሄው፡፡ ኢትዮጵያ ኢሕአዴግ ከመጣ ወዲህ በዚህ አቅጣጫ ምን ያህል ርቀት ሄዳለች? በዜና ምን ተዘገበ? በእቅድ ያደረገው የመስኖ ልማታችን ምን ያል ነው? ገንዘብ ብቻ አይደለም፡፡ ምን ያህል ግድብ የመስራት አቅም ገንብተናል?

በእርግጥ መስኖ ለማልማት የግድ አባይ ላይ ግድብ መስራት አይጠይቅም፡፡ ብዙ ወንዞች አሉ በእኛ አቅም የሚገነቡ፡፡ ነገር ግን በዚህ ዙሪያ ባለፉት 18 አመታት ምን ተሰራ? እስከ አሁን ድረስ ለማኝ የሆነውም በዚህ ዙሪያ ጥሩ ፖሊሲ ስለሌለን ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት የተለያዩ የኃይል ማመንጫዎችን እየሰራ ነው፡፡ ጥሩ ነው፡፡ በኃይል እራሳችን መቻልም ጥሩ ነው፡፡ በመስኖ እራስን ለመቻል በ10 አመት ይሄን ያክል የመስኖ ልማት እናለማለን ብሎ ቁርጥ ያለ አቋም መያዝ ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዩ የአቅም ብቻ ሳይሆን ጠበቅ ያለ ሀገራዊ አቋም እንዲሁም የረጅም ጊዜ እይታ ያለው፣ በየአመቱ እየተደመረ የሚሄድ ጉዳይ መሆን አለበት፡፡ በእርግጥ ብዙ የተነገረለት እስከ አሁን ውጤት ላይ ያልደረሱ ጅምሮች አሉ፡፡ ያም ሆኖ ይሄን ብቻ ነው ልማታዊ መንግሥት ማድረግ ያለበት? እኔም እያለሁ የመስኖ ጉዳይ ኢሕአዴግ ውስጥ ብዙ አነጋግሯል፡፡ ብዙ ያጨቃጨቀን ጉዳይ ነበር፡፡ ውሃን ማቀብ ያደረገ ግድብና መስኖ ማስፋፋት ላይ ያተኮረ የልማት አቅጣጫ መከተል አለመከተል፣ በአንድ በኩል ገንዘብ የለንም ብሎ መልፈስፈስ በሌላ አቅጣጫ ያጨቃጨቀን ጉዳይ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን ትላልቅ የኃይል ማመንጫዎች ቢገነቡም በመስኖ ግንባታ ግን ብዙ እየታየን አይደለም፡፡ በዝናብ ላይ የተንጠለጠለ ልማት ካለ ደግሞ ትንሽ እክል ሲያጋጥም ወደ

ኋላ መመለስ ይፈጠራል። በዚህ ጉዳይ ላይ ኢሕአዴግ ብዙ እድል አባክኗል። ወደ ፊት ቀስ በቀስ ኢሕአዴግ እየተንፏቀቀ እውን ያደርገው ይሆናል። ነገር ግን ይሄንን ያልተመለሰ ነገር ላይ ቁርጠኛ መሆን የግድ ይላል። የአባይ ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ ኖረም አልኖረም፤ ግብጾችና ሱዳኖች ጋር ስምምነት ኖረም አልኖረም የራሳችንን አቅም ገንብተን ልንሄድ በምንችለው አቅም ሰፋፊ መስኖዎችን ማልማት አለብን ብሎ የመሄድና ቁርጥ ያለ ደፋር አቋም ያስፈልጋል። አባይን በመገደብ ብቻ ሳይሆን ብዙ ወንዞች አሉን እነሱንም ማየት ያስፈልጋል።

**<u>ሰንደቅ</u>፡-** **በተቃዋሚዎች በኩል ሰበርካታ ጊዜያት «የብሔራዊ እርቅ» ጥያቄ በተደጋጋሚ ይነሳል። በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል ያሉ ሁሉ፣ እርቅ ካደረጉ በኋላ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደ አዲስ መጀመር አለበት የሚሉ አሉ። በኢሕአዴግ በኩል ከመጀመሪያው ጀምሮ ይሄንን አቋም ሲቃወም ቆይቷል። በአጠቃላይ እርስዎ ይሄንን እስካሁን ሲታረቅ ያልቻለን አቋም እንዴት ያዩታል?**

**<u>አቶ ስዩ አብርሃ</u>፡-** እርቅም በለው፤ ድርድርም በለው የኃይል ሚዛን መሆኑን መሳት የለብንም። በስልጣን ላይ ያለ ገዢ ፓርቲ ከተቃዋሚዎች ጋር ለመደራደር ወደ እርቅ ለመምጣት ከጥሩ የሀገር ፍቅር እና ነገሮችን በበጐነት በማየትና በመገንዘብ ቅን ልቦና ከመኖሩ ባሻገር ተመጣጣኝ የኃይል ሚዛን መኖር አለበት። በእርግጥ የሀገር ፍቅር ካላ፣ ቅን ልቦና ካለን ነገሮችን ለማስተካከል ኃይልም አያስፈልግም።

የሀገር ፍቅር ካለ ቅን ልቦና ካለ ብለው በቅን ልቦና ለመነጋገር የሚመጡ ፓርቲዎችም ሆነ ፖለቲከኞች አሉ። ገና ከሩቁ አደጋውን አይተው፣ የሚያስከፍለውን ዋጋ አይተው እርቅ ብለው የሚመጡ አስተዋይና ብልህ ሰዎች ይኖራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ብዙ ጊዜ ካለመገኘቱ ጋር በተያያዘ የሚኖረው እርቅ እና ሠላም በምን መልኩ ሊመጣ ይችላል የሚለውንም ማየት ያስፈልጋል። ከእርቅና ከድርድር በመለስ ሊመጣ የሚችለው እርቅ በኃይል ሚዛን ነው። ተቃዋሚዎች መጠንከር አለባቸው። መተባበር አለባቸው። ኃይል መሆን መቻል አለባቸው። ሚዛን የሚደፉ መሆን ይገባቸዋል። ህዝብ መያዝ ይኖርባቸዋል። የኃይል ሚዛን ስል ከላይ የጠቀስኳቸውን ማለቴ ነው። ከላይ የጠቀስኳቸው ነገሮች ካሉ ዘንድ ሁሉም ወገኖች መውጫው መንገድ እርቅ ወይም ድርድር መሆኑን ይገነዘባሉ። ገዢው ፓርቲ ሳይቀር መንገዱ እርቅና ድርድር መሆኑን የሚገነዘብበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ያኔ ብሔራዊ እርቅ ይመጣል።

እኔ ስለ ኢትዮጵያ ብሔራዊ እርቅ ብዙ ኢትዮጵያውያን መጨነቃቸው ተገቢ ነው እላለሁ። ስለ ብሔራዊ መግባባት መጨነቅ ይገባናል። ገዢው ፓርቲ ልቦናው ለዚህ እንዲከፈት መጠየቅና መወትወት ተገቢ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ይሄንን ለማሳካት ይቻል ዘንድ ተቃዋሚዎች ደግሞ ሚዛን ሊደፉ የሚችሉበት ደረጃ ላይ ማምጣት አለባቸው። ሁኔታውን የሚጠይቀውን ያህል ክብደት እና ስፍራ ሊኖራቸው ይገባል።

**<u>ሰንደቅ</u>፡-** **ተቃዋሚዎች ወደ ኃይል ሚዛን መድፋት የሂሳብ ስሌት ሲመጡ የሚችሉት እንዴት ነው?**

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>:-** ገዢው ፓርቲ በስልጣን ላይ ለመቆየት ይፈልጋል:: በመድበለ ፓርቲ ስርአት እቀበላለሁ ብሎ በሕገ መንግሥቱ ቢደነግግም «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የተባለው ፕሮግራሙ ግን የአንድ ፓርቲ የበላይነትን ማስጠበቅ ነው የሚለው:: ስለዚህ በኢሕአዴግ ፕሮግራምና ከሕገ-መንግሥቱ መካከል ቅራኔ አለ:: ኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥቱን አከብራለሁ ይላል:: ነገር ግን መልቲ ፓርቲ ሲስተም እንዳይኖር የሚያደርግ መስመር ይዞ ይገኛል:: ይህም ሆኖ «አልፈጥርም» አለን ብለው ተቃዋሚዎች ቁጭ ብለው ያለቅሳሉ...? «ተከለከልኩኝ» ብለው እጅ አጣጥፈው ይቀመጣሉ...? ያለውን ሁኔታ ግን ታግሎ መቀየር ነው:: አለመታደል ሆኖ ያለው ሁኔታ ተደራጅቶ ለመታገልና ኃይል ሆኖ ለመውጣት አስቸጋሪ ነው:: አንድ እህል የማያበቅል መሬት ቢሰጥህ እህል እንዲያበቅል ለማድረግ ትታገላለህ እንጂ ተትቶ አይኬድም:: ስለዚህ ታግሎ መቀየር ነው:: እንደተባለው የፖለቲካ ምህዳሩ በጣም አስቸጋሪ ነው:: ኢሕአዴግ ደግሞ ይበልጥ አስቸጋሪ እያደረገው ነው:: በሕግ ላይ ሕግ እያወጣ የበለጠ አስቸጋሪ አድርጎታል::

**<u>ሰንደቅ</u>:-** አሁን በሠላማዊ ትግል ያሉትም ይሁን ከሠላማዊ ትግል በውጪ ሆነው እንታገላለን የሚሉት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች በትክክል የኢሕአዴግን ፖሊስና ፕሮግራም አውቀውና ተረድተውት የሚቃወሙ ይመስሉዎታል?

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>:-** አልተረዱትም ለማለት አስቸጋሪ ነው:: ምን ያህል ተረድተውታል የሚለውም ከፓርቲ ፓርቲ ይለያል:: ኢሕአዴግ ስልጣን ሲይዝ የነበረው ሁኔታና አሁን ያለው የኢሕአዴግ አቋም አንድ አይደለም:: መጀመሪያ ተስፋ ሰጪ ነገሮች ነበሩ:: ወደ ኋላ ላይ ግን ይሄ ነገር እንደማይሆን የበለጠ ግልፅ የሆነበት ሁኔታ ነው ያለው:: ስለዚህ ከመጀመሪያው ጀምሮ ሁሉም ተቃዋሚዎች ኢሕአዴግን ተረድተውታል ማለት አይቻልም:: ይረዳሉም ብሎ ማለትም አይጠበቅም:: ከጊዜና ትምህርት እንዲሁም በተሞክሮ የሰው ግንዛቤ እየሰፋና ጥልቀት እያገኘ ስለሚሄድ በዛ ደረጃ ሊታይ ይችላል::

**<u>ሰንደቅ</u>:-** እርስዎ በትብብር መድረኩ የፓርቲዎችና የግለሰብ ስብሰብ በመሳተፍ ላይ ኖዎት:: ከስብስቡ ጋር ከተቀሳቀሱም በኳላ ባቀረቧቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ተቃዋሚዎች አንድ በሚያደርጋቸው አቋሞች እንዲሰባሰቡ እየጠየቁ ነው:: በተለይም በብሔርና በህብረ ብሔር የተደራጁ ኃይሎች ወደ «አማካይ ስፍራ» እንዲመጡ እየጠየቁ ነው:: በሌላ በኩል ኢሕአዴግ «ትምክህተኞች (ነፍጠኞች)» እና «ተገንጣዮች» ከሚላቸው ኃይሎች በተለይ ትክክለኛ ግንባር ፈጥሮ ሀገሪቷን በ«ልዩነት አንድነት» በመምራት ላይ እንዳለ ይታወቃል:: እርስዎ «አማካይ ስፍራ» የሚሉት የፓርቲ አደረጃጀት ከኢሕአዴግ በምን ይለያል?

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>:-** ኢሕአዴግ እኮ ዴሞክራቲክ መብቶችንና የዜጎችን መሠረታዊ መብቶች አያከብርም:: ኢሕአዴግ የብሔር ብሔረሰቦችን መብቶችንም አያከብርም:: ኢትዮጵያ ውስጥ ፌዴራሊዝም አለ ተባለ እንጂ በተጨባጭ በኢሕአዴግ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚንቀሳቀሱ ክልሎች ነው ያሉት:: ስለሆነም በመሠረታዊነት የኢሕአዴግ አገዛዝ

ዴሞክራሲያዊ አይደለም:: ከዜጐች መብት በተለይም ከግለሰብ መብት የቡድን መብትና ሀቀኛ ፌደራሊዝም መገንባት ረገድ ቢታይ የኢሕአዴግ ስርአት በብዙ መልኩ ከፈተናው የወደቀ ወይም ወደ ኋላ የቀረ ነው ለማለት ይቻላል:: ስለዚህ እነዚህ በሙሉ መስተካከል አለባቸው:: ሰብአዊ መብቶች፣ የዜጐች ዴሞክራሲያዊ መብቶች የመናገር፣ ሀሳብን የመግለፅ፣ የመደራጀት፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የመቃወም፣ ገለልተኛ ዳኛ ባለበት መወዳደር እነዚህ ሁሉ በኢሕአዴግ ስርአት ጥያቄ ውስጥ ያሉበት ሁኔታ ነው ያለው::

ለምሳሌ ትግራይ ውስጥ ትግርኛ የሚናገር የክልሉ ፕሬዝዳንት ስላለ፣ የክልሉ ፓርላማ ስላለና የክልል ባንዲራ ስላለ የትግራይ ህዝብ መብት ተከበረ ማለት አይደለም:: እና በምንም መልኩ የግልም በለው የቡድን መብቶች እየተጣሱና ብዙ ነገር ወደ ኋላ የተመለሰበት ሁኔታ ስላለ ይሄ መስተካከል አለበት::

ስለዚህ መብቶች በትክክል እንዲከበሩ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይሄንንም እውን ለማድረግ ተመሳሳይ የፖለቲካ አቋሞች ወደ አንድ መሰባሰብ ይኖርባቸዋል:: የብሔር ድርጅቶች የብሔርን መብት እናስከብር ስላሉ የኢትዮጵያ አንድነት ስጋት ተደርገው መቆጠር የለባቸውም:: ኢትዮጵያዊነታቸውን ተቀብለው በኢትዮጵያ የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲኖር የሚቆሙና የሚታገሉ ህብረ ብሔራዊ ድርጅቶችም አሉ:: ስለዚህ እነዚህ ደግሞ የብሔር ጥያቄ ያነሱትን እንደ ስጋት ሊያዩ አይገባም:: ከመገንጠል በመለስ ያሉት መብቶች ቢከበሩ ለኢትዮጵያ ሠላም፣ መረጋጋት ወዳጅነትና ፍቅር ይመሰርታል እንጂ ጠንቅ አይሆንም:: ስለዚህ ከመገንጠል በመለስ ያሉትን መብቶች እንዲከበሩ የሚታገሉ የብሔር ድርጅቶች ኢትዮጵያዊ ናቸው:: እነዚህን ኢትዮጵያውያን አይደላችሁም ብሎ ለኢትዮጵያ አንድነት ስጋት አድርጐ ማቅረብ ትክክለኛ አይደለም::

በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ስለ ጋራ እኛነታችን የሚጨነቁ ፓርቲዎች አሉ:: የዜግነት መብቶች እንዲከበሩ የሚጨነቁ፣ አንዳንድ የመገንጠል ጥያቄዎች ሲነሱ የሚሰጉ አሉ:: እነዚህ ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ተገቢ የሆነ ሕጋዊ ጥያቄና ስጋት አላቸው:: እነዚህን አይነት ዴሞክራቲክ ኢትዮጵያውያን ትምክህተኞች ተብለው የሚወገዙበት ሁኔታ የለም:: ነገር ግን እነዚህ እያሉም ቢሆን ከእነዚህ ደግሞ ወደ ጫፍ የወጡ የብሔርን ጥያቄ ሁሌም የሚያጣጥሉ አመለካከት ያላቸው አሉ:: እነዚህ በብሔር ተደራጅተው መገንጠልን ብቻ ከሚፈልጉት ጋር ሊነፃፀሩ የሚችሉ ናቸው:: በብሔር መደራጀትን የሚያጣጥሉ ኃይሎች ኢትዮጵያን ወዴት ሊወስዷት እንደሚችሉ አይታወቅም:: ወደ ድሮ ስርአት ይሁን ወደ የት እንደሆነ ያለየ አቋም ነው የያዙት:: ያም ሆኖ ከሁለቱም በኩል ያሉትን ጫፎች አስወግደው ተገቢና ሕጋዊ የሆነ የኢትዮጵያን አንድነት ከመገንጠል በመለስ ገቢራዊ እንዲሆን የሚታገሉ ኢትዮጵያውያን አሉ:: በተለይም በኢትዮጵያ አንኳር ነጥቦች ማለትም በኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት፣ በዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት መከበር፣ በሕግ የበላይነት መከበር፣ በኢትዮጵያ ልማትና የጋራ ጥቅሞች የማይለያዩ ከሆነ ህብረ ብሔርና ብሔራዊ አደረጃጀት አብረው

የማይሰሩበት ሁኔታ የለም። እኔም አማካይ ስፍራ ያልኩት ለዚሁ ነው። ይሄም ከኢሕአዴግ በእጅጉ የሚለይ አስተሳሰብና አመለካከት ነው።

**<u>ሰንደቅ</u>፡-** **እርስዎ ታዋቂ ሰው ቢሆኑም በአሁኑ ወቅት በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ የሉበትም። እንደ እርስዎ ያለ ሰው ወይ የፖለቲካ ፓርቲ አቋቁሞ ይንቀሳቀሳል አለበለዚያ ደግሞ የሲቪል ድርጅት መስርቶ ሲሰራ ይችላል። እርስዎ ከሁለቱ አንዱን ለመሞከር ያልፈለጉት ለምንድነው?**

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>፡-** በእርግጥ የገባሁበት ፓርቲ የለም። ነገር ግን በፖለቲካ ዙሪያ እየሰራሁ ነው። በ«መድረኩ» ዙሪያ እየሰራሁ ነው። በ«መድረክ» ዙሪያ ሆኜ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ማድረግ የምችለውን አስተዋፅኦ አላቋረጥኩም። ከእስር ከተፈታሁም በኋላ ብዙ ጊዜ አላጠፋሁም። ለምንድነው የራስህን ፓርቲ ያልመሰረትከው ለሚለው፤ ቢያንስ እስር ቤት ብዙ ጊዜ ቆይቻለሁ። ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ በኢትዮጵያ ያሉት ብዙ ፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው። በሀገሪቱ ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢኖሩም በሀገራዊ አንኳር ጉዳዮች ላይ መግባባት የተደረሰበት ሁኔታ አይደለም ያለው። በዚህ ምክንያት የፓርቲዎች መበራከት ተከስቷል።

ስለሆነም ብዙ ጊዜ ሳይወስድ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ መደረግ ያለበት ነገር መፈፀም አለበት። በፓርቲ የተደራጁም ያልተደራጁ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ማድረግ ያለባቸው ጉዳይ ቢኖር ዋና ዋና የሆኑ ፖለቲካዊ ነጥቦችን ለይቶ በነዛ ነጥቦች ላይ መግባባትን መፍጠር ነው። ይሄንን ደግሞ ሳደርግ ቆይቻለሁ። ፍሬ ይኖረዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። መድረኩ ውስጥ ያሉት ፓርቲዎች በርካታ የጋራ አቋሞችን ይዘው በትብብር የሚሰሩበት ሁኔታ ይፈጠራል ብዬም እገምታለሁ። ይሄ ደግሞ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ትልቅ ... ትልቅ ... ስኬት ይሆናል። እኔ በፓርቲ ውስጥ ኖርኩም አልኖርኩም ትልቅ ፖለቲካዊ ፋይዳ ይኖረዋል ብዬ ነው የምገምተው።

ስለ እኔ በፓርቲ መግባት አለመግባት በእርግጥ በዚህ ጊዜ የቱ ነው የሚበጀውና ውጤታማም የሚሆነው ከመግባባት አንፃር የትኛው ነው ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የሚለው ካልሆነ በስተቀር፤ ግለሰቦች ያለ ፓርቲ ተሳትፎ ዝም ብለው በግል ይቀጥላሉ ማለት አይደለም። ስለዚህ የያዝነውን ስራ ዳር የማድረስ ስራ እንዳለ ሆኖ ወደፊት የሚታይ ነው።

**<u>ሰንደቅ</u>፡-** **የመድረኩ እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላ ከመድረኩ ጋር አብሮ ላለመስራት የሚነሱ ተቃውሞዎች አሉ። በተለይም አንድነት ፓርቲ አካባቢ ከመድረኩ ጋር አብሮ የመስራት ጥያቄ ላይ የአመለካከት መሳሳብ እየታየ ነውና ይሄ ስሜት ጊዜአዊ ነው ብለው ያስባሉ?**

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>፡-** አዎን። ይሄ ነገር ቁምነገር ደርሶ ሲታይ የሰከነ አመለካከት ያለው ሰው ለኢትዮጵያ የሚፈልገው ጠንካራ እና የተባበረ አማራጭ እስከሆነ ድረስ በጋራ ጉዳዮች ላይ መተባበር ያስፈልጋል። አሁን ያሉትም አንዳንድ ያለዩ ስሜቶችና አመለካከቶች ወደ ፊት እርምጃና ውጤት በታየ ቁጥር እነዚህ ያለዩ ስሜቶች እየሰከኑ ይሄዳሉ ብዬ እገምታለሁ። ይሄ ደግሞ በሁሉም ፓርቲ ቤት ያለ ጉዳይ ነው። ደረጃው ሊለያይ ይችላል። በቆዩ አስተሳሰቦች ዙሪያ የተሰባሰቡ ፓርቲዎች ናቸው ያሉት። የቆዩ ስሜቶች እና ቁስሎች አሉ። ይሄን የሚያነቃንቅ ነገር ሲመጣ የሽግግር ጊዜ ይኖራል። የአስተሳሰብ ሽግሽግ እስኪኖር ድረስ

የሚፈጠር እዛም... እዛም... የሚመር ነገር ይኖራል:: እየተቀራረብን ስንሄድ፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮች እየለዩ ሲሄዱ፤ ከስሜት አልፈው የሚጨበጡ፣ የሚዳሰሱ ፖለቲካዊ አቋሞች እየሆኑ ሲመጡ አብዛኛዎቹ ጉዳዮች እየሰከኑ ይመጣሉ:: እና በአንድ ፓርቲ ብቻ ያለ ችግር ባይሆንም ገኖ የወጣው በተወሰኑ ፓርቲዎች ሊሆን ይችላል:: አንድነት አካባቢ አንዳንድ ስሜቶች እንዳሉ እሰማለሁ:: ነገር ግን አንድነቶችም ቢሆኑ በመሠረተ ሀሳብ ደረጃ «መድረክ ውስጥ መግባት ስህተት ነው» ሲሉም አልሰማሁም:: መሰባሰብን ይቀበላሉ:: ነገር ግን ይሄ ይውጣ፣ ይሄ ይቀነስ ሊሉ ይችላሉ:: አብዛኛው የኢትዮጵያም ሕዝብ ፖለቲከኞች በአንድ ላይ መሰባሰባቸውን፣ መወያየትና መመካከራቸውን በበጐ ተስፋ ነው የሚያየው:: ስለዚህ ይሄ በጐ ተስፋ፤ ተስፋ ከመሆን አልፎ ቁም ነገር ላይ እንዲደርስ ማድረግ ነው:: ጅምሩ ቁም ነገር ላይ ደርሶ ሲታይ ብዙ ሰዎች ያደረባቸው ስጋት ሊቀረፍላቸው ይችላል::

**<u>ሰንደቅ</u>:-** **የመድረኩ የፖለቲካ አስተሳሰብ በዲያስፖራውስ በኩል ምን ያህል ተቀባይነት ይኖረዋል?**

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>:-** እኔ ስለዲያስፖራው የማየው ብዙ ገፅታዎችን ቢሆንም፤ በትክክል ይሄንን እንቅስቃሴ የሚደገፉ ወገኖች አሉ:: እነሱም ቢሆኑ «እንሰባሰብ በውስጣችን ያለውን ጥላቻ እና የቁርሾ ስሜት አስወግደን እንመካከር» የሚሉ በርካታ ምሁራን አያለሁ:: መሰባሰቡን ባይቃወሙም ስጋት ያላቸውና ጥያቄዎችን የሚያነሱም አሉ:: ስለዚህ ዲያስፖራው በዚህ ጉዳይ ላይ ወጥ አመለካከት አለው ብሎ ለመናገር አስቸጋሪ ነው:: ዲያስፖራው ያለው ኢትዮጵያዊ በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሰብአዊ መብት እንዲከበር አብረን መስራት አለብን፣ እርስ በርስ መናቆር ይብቃ፣ ለራሳችን እራሳችን ጠላት መሆን ይብቃ ብለው የሚገፋፉ ወገኖች አሉ:: ይሄ ደግሞ በጐ ነገር ነው:: በእርግጥ ጫፍ የረገጡ አስተሳሰቦች ደምቀው የሚወጡበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል:: ያም ሆኖ ምሁራን ጉዳዩን ሰከን ብሎ የማየትና «እንሰባሰብ» የማለት ሁኔታ ስላለ ዲያስፖራው በአንድ ገፁ ብቻ መነበብ የለበትም::

**<u>ሰንደቅ</u>:-** **ሕገ-መንግሥቱ በሚያዘው መሠረት በ2002 የመድብለ ፓርቲ ምርጫ ይካሄዳል:: ሆኖም በገዢው ፓርቲ መጠናከርና በተቃዋሚዎች መዳከም ምርጫው ከወዲሁ ፉክክር የማይታይበት እንደሆነ በመገለፅ ላይ ይገኛል:: በዚህ ላይ እርስዎ ምን ይላሉ?**

**<u>አቶ ስዬ አብርሃ</u>:-** ገዢው ፓርቲ በጣም ተጠናከረ የሚባለውን ነገር በቅድሚያ ማየት ያስፈልጋል:: ተጠናከረ ስንል የውሃ ልኩን ማየት የኖርብናል:: አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ጠንካራ ወይም ደካማ ተብሎ የሚባለውና የሚለካው በያዘው የፖለቲካ ፕሮግራም ነው:: በሚያራምደው የፖለቲካ መስመር ነው:: እቆምለታለሁ የሚለው አቋሞች ናቸው:: አምንባቸዋለሁ የሚላቸው ፖሊሲዎችም ናቸው::

በሁለተኛ ደረጃ በህዝብ ያለው በጐ ስሜት ነው:: ህዝብ «ይመራኛል» ብሎ የሞራል አክብሮትና ተቀባይነት ሊሆን ይችላል:: ሦስተኛው የድርጅቱ አባላት ጥንካሬ የአቋም ጥራትና፣ ፅናት፣ ታማኝነትና ቆራጥነት ሲኖር ነው:: በአራተኛ ደረጃ የገንዘብ አቅም ጥንካሬ ሲኖር ነው::

እና በነዚህ መመዘኛ ኢሕአዴግ ጠንካራ ነው የምትሉት በየትኛው መመዘኛ ነው? በእርግጥ ኢሕአዴግ በስልጣን ላይ ያለ ፓርቲ ነው፡፡ እና ከልካይና አፋኝ ሕጐች እያወጣ በሕገ-መንግሥት የሰፈሩ ድንጋጌዎችን በአሰራርና በመመሪያ አንዳንዴም በአዋጅ እየከለከለ ፍርሃት በማንገስ በኃይል እየኖረ ያለ እንጂ በአቋሞቹ ጥራት እና ብቃት በፖሊሲዎቹ ብቃት አይደለም፡፡ በዚህ ያገኘው ሞራላዊና ፖሊቲካዊ የበላይነት አይደለም እያቆመው ያለው፡፡ አባላት ተብለው የተሰባሰቡት ለኢሕአዴግ ፕሮግራም ነው ወይስ ለጥቅማ ጥቅሙ ነው? በእርግጥ አሕአዴግ የሚደግፉት በእምነት የቆሙለት ሰዎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ የኢሕአዴግ ጥንካሬ ስልጣን በመያዙና የመንግሥት መዋቅሮቹን ተጠቅሞ ፍርሃት በማንገሱና ክልከላ በማበጀቱ ነው፡፡

እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ፓርቲዎች አቅማቸውን እንዳይገነቡ የመከልከል ችሎታ ያለው ፓርቲ በመሆኑ ነው፡፡ የኢሕአዴግ ጥንካሬ ጠንካራ ተቃዋሚዎች ካለመኖራቸው ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው፡፡ በእርግጥ ይሄ ነገር ምርጫ ላይ ሲመጣ ህዝቡ ምርጫ ምረጥ ተብሎ እንደ ግብር መክፈል ሆኖ ሊመረጥ ይችላል፡፡ ኢሕአዴግን መረጠ ማለት ግን አይደለም፡፡ ኢሕአዴግ ከተፎካካሪዎቹ ተወዳድሮና በልጦ ተገኝቶ ተመርጠ ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ አሁን ያለው ፖለቲካዊ ሁኔታ ሲታይ ተቃዋሚዎች ለሚመጣው ምርጫ ምን ያህ ብቁ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ? የሁሉም ጥያቄ ነው፡፡ ሂደቱ በዚሁ ከቀጠለ እንግዲህ ምርጫው ምርጫ አይሆንም ማለት ነው፡፡ እንደሚያዝያው 2000 የአካባቢ ምርጫ «97 በመቶ ህዝብ መረጠኝ» ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ አሕአዴግ ምርጫውን ለውድድር ከከፈተው ግን ነገሩ ሌላ መልክ ይኖረዋል፡፡ እና ምርጫ 2002ን ኢሕአዴግ ክፍት ያደርገዋል ወይም ተቃዋሚዎች ጠንክረው ያስከፍቱታል፡፡ በአጭር ጊዜ ግን ይሆናል ወይ የሚለው አጠያያቂ ይሆናል፡፡ ዋናው ነገር አሁን ተጀምሮ ያለው የተቃዋሚዎች መቀራረብ ለአሁኑ ምርጫ ሊደርስም ላይደርስም ይችላል እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም፡፡ ባይደርስም ግን ወደ ፊት በአንድ ወቅት ይሄ ነገር ፍሬ አፍርቶ አንድ ውጤት ሊመጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ አሁን የተጀመረው ነገር ከአንድ ምርጫ ጊዜ ጋር መያያዝ የለበትም፡፡ እጅን አጣምሮ ቆይቶ ምርጫ ሲመጣ የመሰባሰብና ምርጫው ሲያልቅ የመበታተን ጨዋታ ማብቃት አለበት፡፡ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ከተፈለገ ምርጫው ተደርጐ ከምርጫውም በኋላ መቀራረቡ ይቀጥላል፡፡ ይሄ ከሆነ መጨረሻ ላይ አንድ ውጤት ይገኛል ብዬ ነው የማስበው፡፡

<u>**ሰንደቅ**</u>**፡-** ኢሕአዴግን ለሁሉም ችግሮች ተጠያቂ አድርጐ ማቅረብ አንዱ የተቃዋሚዎች ችግር እንደሆነ ይገለፃል፡፡ በዚህ ረገድ ከደርግ ውድቀት በኋላ ኢሕአዴግ ምንም ስኬት አላስመዘገበም ብሎ መደምደም ይቻላል? በቅርቡም ስለዚህ ጉዳይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ተጠይቀው ኢሕአዴግ ያስገኘው ስኬት የመጠን ብቻ ሳይሆን አብዮታዊም ጭምር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በዚህ ረገድ እርስዎ ምን ይታየዎታል?

<u>**አቶ ስዬ አብርሃ**</u>**፡-** ደርግ ወድቆ ኢሕአዴግ ስልጣን ከያዘ ወዲህ ለውጥ አልመጣም የሚል እምነት የለኝም፡፡ እኔ መሆን ካለበት ደረጃ ተነስቼ እንጂ ወደ ኋላ እያየሁ፣ ሃያ አመት

ተመልሼ ከሃያ አመት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው «እሻላለሁ» ብሎ ንፅፅር ማድረግ ትክክለኛ አይደለም። «ከደርግ የተሻልኩ ቆንጆ ነኝ» ብሎ ኢሕአዴግ ቢናገር ንፅፅሩን አልደገፈውም። የሰነፍ ንፅፅር ሆኖ ይታየኛል። ደርግ እኮ ሰው በላ ስርአት በመሆኑ ሁላችንም ታግለን ጥለነዋል። የኢትዮጵያ ህዝብም ታግሎ ጥሎታል። ከእንግዲህ ደርግን አይናፍቅም። እና «ከደርግ እሻላለሁ» ... «ከኢሳያስ እሻላለሁ» ... «ከመንግሥቱ ኃይለማርያም እሻላለሁ» ... ብሎ ማወዳደር እውነት ለመናገር እራስን ማዋረድ ነው።

ኢሕአዴግ አሁንም ከኢሰፓ እና ከሻአቢያ ጋር እራሱን የሚያነፃፅር ከሆነ ብዙ ርቀት እንዳልተጓዘ እራሱ ስለ እራሱ እየመሰከረ ነው ማለት ነው። እና የኢሕአዴግ መንግሥት መለኪያዎቹን እየነገረን ነው ማለት ነው። ሌላ መለኪያ አላመጣም ወይም የዘመኑን መለኪያ አላስቀመጠም ማለት ነው። በዘመኑ መለኪያ እራሱን መፈተሽ ስለማይፈልግም ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በዘመኑ መለኪያ እንዲለካው ስለማይፈልግ ከኢሳያስና ከመንግሥቱ ኃይለማርያም እኔ እበልጣለሁ ብሎ የቁንጅና ውድድር ነው እየተካሄደ ያለው። እኔ ብሆን ግን ኢሕአዴግንና መንግሥቱ ኃይለማርያምን አላነፃፅራቸውም።